የአማራ ክልል
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች

## የችሎት ሥርዓት

## መመሪያ ቁጥር 21/2018

ሕዳር 1 ቀን 2018ዓ.ም

ባህርዳር

# የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የችሎት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ.ም

በግልጽ ችሎት የመዳኘት መብት እውን የሚሆነው ግልጽነትን የሚያሰፍኑ የሕግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን በመዘርጋት መሆኑን በማመን፣

ፍርድ ቤቶች በዕለት ተዕለት የዳኝነት ሥራ አካሄድ የሚተገብሯቸው አሰራሮች ከቦታ ቦታ፣ እንዲሁም ከችሎት ችሎት የሚለያዩ እና ወጥነትና ተገማችነት የሚያንሳቸው በመሆኑ ወጥነት እና ተገማችነትን የሚያሰፍን የችሎት ሥርዓት ማስፈን አስፈላጊ መሆኑን በማመን፣

ግልጽነት፣ ወጥነት እና ተገማችነት ያለው የችሎት ሥርዓትን በማስፈን የፍርድ ቤቶችን እና የዳኝነት ሙያን ክብር ይበልጥ ማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ኅብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለው አመኔታ ከፍ እንዲል እና የባለጉዳዮችን እርካታ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የችሎት ሥርዓትን ማክበር እና ማስከበር አስፈላጊ መሆኑን በማመን፣

በአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 አንቀጽ 64(2) እና አንቀጽ 36(2)(በ) መሰረት ይህ የችሎት ሥርዓት መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የችሎት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **«ፍርድ ቤት»** ማለት በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የተዋቀሩትን ጠቅላይ፣ ከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤቶችን የሚመለከት ነው፡፡
2) **«ጉባኤ»** ማለት ዐቢይ እና ንዑሳን ጉባኤዎችን በመያዝ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች የተደራጀው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነው፡፡
3) **«የፍርድ ቤት አመራር»** ማለት የጠቅላይ፣ የከፍተኛ እና የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንቶች እና ምክትል ፕሬዝደንቶች ማለት ነው፡፡
4) **«ዳኛ»** ማለት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ውስጥ የዳኝነት ተግባራትን እንዲያከናውን በምክር ቤት የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ሲሆን ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል ረዳት ዳኛንም ይጨምራል፡፡
5) **«የጉባኤ ተሿሚ»** ማለት እንደአግባብነቱ በዐቢይ ወይም በንዑስ ጉባኤዎች የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡
6) **«የአስተዳደር ሰራተኛ»** ከዳኛ እና የጉባኤ ተሿሚ ውጭ ያለ ማንኛውም የፍርድ ቤት የሥራ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ነው፡፡
7) **«ችሎት»** ማለት ዳኛ ወይም ዳኞች ጉዳዮችን የሚያከራክሩበት፣ ምስክሮች የሚሰሙበት፣ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጡበት እንዲሁም ውሳኔ የሚያነቡበት የችሎት ማስቻያ ቦታ፣ ስፍራ ወይም የዳኞች ጽሕፈት ቤት ማለት ነው፡፡
8) **«የችሎት ፖሊስ»** ማለት የችሎት ሥርዓት እንዲያስከብር የተመደበ የፖሊስ ባልደረባ ማለት ነው፡፡
9) **«የችሎት ሥርዓት አስከባሪ»** ማለት የችሎት ሥርዓት የሚያስከብር የአስተዳደር ሰራተኛ ነው፡፡
10) **«ዐቃቤ ሕግ»** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልል ፍትሕ ቢሮ ማቋቋሚያ ሕግ መሰረት የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ሲሆን በሌሎች የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ዐቃቤ ሕግ ተብሎ የተሾመ የተፈጥሮ ሰውን ይጭምራል፡፡
11) **«ጠበቃ»** ማለት የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ስልጣን ካለው አካል ፈቃድ ያገኘ የሕግ ባለሙያ ሲሆን የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖረው የግል ድርጅቶችን፣ የልማት ድርጅቶችን እና ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ወክሎ የሚከራከር ነገረ ፈጅን እና ተከላካይ ጠበቆችን ይጨምራል፡፡

12) **«አስተርጓሚ»** ማለት የሀገር ውስጥ ወይም የውጪ ወይም የምልክት ቋንቋ በብቃት መስማትና መናገር የሚችል እና ይህን የመተርጎም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው፡፡

13) **«ባለጉዳይ»** ማለት በተያዘው ክርክር ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ አመልካች፣ ተጠሪ፣ ዐቃቤያነ-ህግ፣ ጠበቃ፣ አቤቱታ አቅራቢ፣ ተጠሪ፣ የክርክር ጣልቃ ገቦች፣ ውሳኔ ለመቃወም ወደ ክርክር የገቡ ወይም ይግባኝ ባይ እና መልስ ሰጪን ወይም ፍርድ ቤት የቀረበ ማንኛውም ባለጉዳይ ማለት ነው፡፡

14) **«ምስክር»** ማለት በክስ ወይም መልስ ላይ በማስረጃነት የተጠቀሰ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በችሎት ፊት ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ሰው ማለት ሲሆን የባለሙያ ምስክርን ይጨምራል፡፡

15) **«ፖሊስ»** ማለት የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ለመፈፀም ችሎት ላይ የሚቀርብ ፖሊስ ሲሆን የማረሚያ ቤት ፖሊስ፣ ፌደራል ፖሊስ፣የጉምሩክ መስሪያ ቤት ፖሊስ እና ትራፊክ ፖሊስን ይጨምራል፡፡

3. **የጾታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው በተመሳሳይ ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በችሎት ወይም እንደአግባብነቱ በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በተገኘ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ዓላማ እና ግብ

5. **ዓላማ**

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1) የፍርድ ቤትን እና የዳኝነት ሙያን ክብር ማስጠበቅ፣
2) ግልጽ፣ ወጥነት እና ተገማችነት ያለው የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ማስፈን፣
3) ኅብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ሊያሳድር የሚገባውን አመኔታ ከፍ ማድረግ፣
4) የባለጉዳዮችን እርካታ ማሳደግ፣

6. **ግብ**

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ግቦች አሉት፡-

1) ፍርድ ቤቶች የሚመሩበትን ግልጽ የችሎት ሥርዓት መዘርጋት፣
2) ሙያዊ ሥነ-ምግባርን በማሻሻል ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፣
3) ወጥነት እና ተገማችነት ያለው ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፣
4) ኅብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን እርካታ እና አመኔታ ከፍ እንዲል ማድረግ፣

## ክፍል ሶስት

## የቅድመ ችሎት እና የችሎት ሥርዓት

7. **የቅድመ ችሎት ሥርዓት**

1) ችሎት ከመጀመሩ በፊት በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በቴሌቪዥን ማሳያ ላይ በዕለቱ የተቀጠሩ መዝገቦች ቁጥር፣ የተቀጠረበት ሰዓት፣ የባለጉዳዮችን ስም፣ የጉዳዩን አይነት እና ጉዳዩ የተቀጠረበት ምክንያት በግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለበት፡፡
2) የችሎቶች፣ የዳኛ ቢሮ፣ የሬጅስትራር ቢሮ፣ መረጃ ዴስክ፣ የአስተዳደር ሰራተኞች ቢሮ ስያሜ ለባጉዳዮች በግልፅ በሚታይ መልኩ በየቢሮዎቹ በሮች ላይ  መለጠፍ አለበት፡፡
3) የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዋና የሥራ ሒደት አስተባባሪዎች፣ የችሎት ሰብሳቢ ዳኞች፣ ሬጂስትራሮች፣ ባለሙያዎች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፍርድ ቤት ሰራተኞች ችሎቱ ስለመፀዳቱ፣ የችሎት አዳራሽ መብራት መስራቱን፣ የዕለቱ መዝገብ

መቅረቡን ፤ የዳኛ አጀንዳ መዘጋጀቱን፣ የዳኞች ስም ያለበት የጠረጴዛ ባጅ መኖሩን፣ ህጎች፣ የችሎት ወረቀት፣ ብዕር፣ የድምፅ መቅረጫ፣ የችሎት መዶሻ እና ለችሎት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግብዓቶች መሰናዳታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

4) በወንጀል ችሎት ዐቃቢያነ-ህግ፣ ጠበቆች፣ ተከላካይ ጠበቆች ባለጉዳዮች እና ሌሎች ሰዎች ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ወደ ችሎቱ አዳሽ ወይም ክፍል ገብተው ከዳኛው ፊት ለፊት ዐቃቤያነ-ህጎች ከችሎቱ በተዘጋጀላቸው ቦታ፣ ጠበቆች እና ተከላካይ ጠበቆች በተዘጋጀላቸው ቦታ ከተጠርጣሪው ጎን፣ ምስክሮች ከዳኞች ከሁለት ሜትር በላይ በሆነ ርቀት ላይ በተዘጋጀ ማረፊያ፣ አስተርጓሚ ከምስክሩ ወይም ከሚያስተረጉመው ሰው ጎን፣ የችሎት ፀሀፊ ከችሎቱ መድረክ ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ እንዲሁም ታዳሚዎች በችሎት በተዘጋጀላቸው ቦታ ስፍራቸውን መያዝ አለባቸው፡፡

5) ለፍትሐ ብሔር ችሎት ከሳሽ በቀኝ በኩል፣ ተከሳሽ በግራ በኩል፣ ጠበቃ በስተግራ ወይም በስተቀኝ ወክሎ ከሚከራከርለት ሰው ጎን፣ ምስክሮች ከዳኞች ከሁለት ሜትር በላይ በሆነ ርቀት ላይ በተዘጋጀ ማረፊያ፣ አስተርጓሚ ከምስክሩ ወይም ከሚረጉምለት ሰው አጠገብ፣ የችሎት ፀሐፊ ከችሎት መድረክ ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ እንዲሁም ታዳሚዎች በችሎት በተዘጋጀላቸው ስፍራ ቦታቸውን መያዝ አለባቸው፡፡

6) ዳኞች ወደ ችሎት ሲገቡ የችሎቱ ሥርዓት አስከባሪ ወይም ፖሊስ በችሎት አዳራሽ ውስጥ የተገኙት ሁሉም ሰዎች ተነስተው እንዲቀበሏቸው በማሳሰብ የመቀመጫ ቦታቸው ሲደርሱ ለዳኞች ወታደራዊ የአክብሮት ሰላምታ በመስጠት ችሎት ውስጥ ወዳሉት ሰዎች በመዞር እነርሱም በምልክት ሰላምታ እንዲቀመጡ ማድረግ አለበት፡፡

7) ችሎቱን እንዲታደሙ የተፈቀደላቸው መገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች በተዘጋጀላቸው ወይም ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ ሆነው ችሎቱን የሚታደሙ ይሆናል፡፡

8) ዳኛው ወይም የችሎት ሰብሳቢ ዳኛው ችሎቱ የዕለቱን የችሎት ሥራ የጀመረ መሆኑን የችሎት መዶሻ በመምታት ማብሰር አለበት፡፡

8. **የችሎት ሥራ መጀመሪያ ሠዓት**

1) የመንግስት መደበኛ የሥራ ሠዓት እንደተጠበቀ ሆኖ የችሎት ስራ ጠዋት 3:00 እና ከሠዓት በኋላ ደግሞ 8:00 መጀመር አለበት

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የችሎት ሥራ መጀመሪያ ሠዓት እንደየ አካባቢው የአየር ሁኔታ ወይም ፀባይ ሊቀያየር ይችላል፡፡

9. **ባለጉዳዮች የሚስተናገዱበት ቅደም ተከተል**

ዳኛው በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ጉዳዮችን በመቅጠር ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገቡ ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት ማስተናገድ አለበት፡፡

10. **የቃለ መሐላ ሥርዓት**

1) ቃለ መሃላ እውነትን በማፈላለግ ረገድ የጎላ ሚና ያለው በመሆኑ ዳኛው ወይም የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ የቃለ መሃላውን ዓላማ እና ውጤት በማስረዳት ተከራካሪዎች ወይም ምስክሮችን ወይም አስተርጓሚዎችን ቃለ መሃላ ማስፈፀም አለበት፡፡

2) ቃለ መሃላ የሚፈጸመው በዳኛ ፊት ሲሆን ለችሎቱ ሊሰማ በሚችል መልኩ በተናጠል መፈፀም አለበት፡፡

11. **ለችሎት ክብር ስለመቆም**

1) በችሎት ሂደት ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ቅጣት፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ሲሰጥ እና ሲነበብ፣ የክስ እና መልስ ቅብብል ሲደረግ፣ ክርክር ሲካሄድ፣ ምስክር ሲሰማ፣ ባለጉዳዩ አቤቱታ ሲያቀርብ ወይም ዳኛው በሚያስችልበት ወቅት ባለጉዳዩ ቆሞ ችሎቱን መከታተል አለበት፡፡



Am/Nat/Regional State Supreme Court North Shoa High Court

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ክርክሩ የሚራዘም ከሆነ አንደኛው ወገን ሲናገር ሌላኛው ወገን፣ በጋራ ከተከሰሱት ወይም ከከሰሱት ሰዎች መካከል ምስክር ከሚያሰማው ወይም ከሚሰማበት ውጪ ያለው ተከሳሽ ወይም ከሳሽ፤ በህመም ወይም በእርግዝና ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት መቆም የማይችል ሰው እንዲቀመጥ ችሎቱን የሚያስችለው ዳኛ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

12. **ድምፅን ከፍ አድርጎ ስለመናገር**

1) ዳኛ ችሎት ሲመራ ለችሎት ታዳሚዎች በሙሉ በሚሰማ መልኩ ድምጹን ከፍ አድርጎ መናገር አለበት፡፡
2) ዐቃቢያነ-ህግ፣ ጠበቆች፣ ተከላካይ ጠበቆች፣ ምስክሮች፣ ተከራካሪዎች እና ባለጉዳዮች ክርክራቸውን ሲያቀርቡ ለዳኛው፣ ለችሎቱ እና ለተከራካሪው ወገን ሊሰማ በሚችል ሁኔታ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው መናገር አለባቸው፡፡

13. **የአለባበስ ሥርዓት**

1) ማንኛውም ዳኛ ችሎት ሲያስችል በፍርድ ቤቱ የተዘጋጀለትን ካባ የመልበስ ግዴታ አለበት፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የተጠቀሰው በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች ወይም የቤተሰብ ወይም የሴቶች ወይም ህጻናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲታዩ ዳኞች ካባ ላይለብሱ ይችላሉ፡፡
3) ዐቃቢያነ-ሕግ፣ ጠበቆች፣ ነገረ-ፈጅ፣ እና ተከላካይ ጠበቆች ከችሎት ውጪ ካባ ለብሰው በችሎት መገኘት ያለባቸው ሲሆን በችሎት ውስጥ ካባ መልበስም ሆነ መቀየር ወይም ማውለቅ አይችሉም፡፡
4) የተጨማደደ እና ንፅህናው ያልተጠበቀ ካባ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት የተከለከለ ነው፡፡
5) ማንኛውም ዳኛ፣ ዓቃቢያነ-ህግ፣ ጠበቃ፣ ነገረ-ፈጅ ወይም ተከላካይ ጠበቃ እንደአግባብነቱ ከካባው ውስጥ ለወንድ ሙሉ ልብስ፣ ሸሚዝ እና ከረባት እንዲሁም ለሴት ሙሉ ልብስ፣ ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ፣ ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ እና ካባው እስከ አንገት ድረስ በቁልፍ ወይም በዚፕ የተዘጋ መሆን አለበት፡፡
6) ማንኛውም ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ፣ ዐቃቢያነ-ሕግ፣ ተከላካይ ጠበቃ፣ የአስዳደር ሰራተኛ፣ ጠበቃ ወይም ፖሊስ የችሎቱን ክብር የሚያቀል ቁምጣ፣ ጥብቆ፣ በጣም አጭር ቀሚስ፣ የተቀደደ ልብስ፣ ቲሸርት፣ የተለያዩ ጽሁፎች ያሉባቸው አልባሳት፣ ሲሊፐር ወይም ሸበጥ ጫማ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት ተከለከለ ነው፡፡
7) ማንኛውም ዳኛ፣ ረዳት ዳኛ፣ ጠበቃ፣ ዐቃቢያነ-ህግ ለወንድ በጣም የረዘመ፣ ድሬድ ወይም ራስታ ፀጉር፣ ለሴት እይታን የሚከለክል የፀጉር አሰራር እንዲሁም ኮፍያ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
8) የችሎት ፖሊስ ለዚህ ሥርዓት የሚውል የደንብ ልብስ እና የችሎት አስከባሪ መሆኑን የሚያሳይ መለያ መልበስ አለበት፡፡
9) ለሬጅስትራር፣ የችሎት ሥነ-ሥርዓት አስከባሪ፣ ድምፅ ቀራጭ እንዲሁም በችሎት መገኘት ያለባቸው የፍርድ ቤቱ ሰራተኞች የችሎቱን ክብር የሚመጥን በፍርድ ቤቱ የተዘጋጀ የደንብ ልብስ መልበስ አለባቸው፡፡
10) የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የተለየ የአለባበስ ሥርዓት እንዲከተሉ ባይገደዱም የደንብ ልብስ የተፈቀደላቸው ሰራተኞች በሥራ ሰዓትና ቦታ የደንብ ልብስ የመልበስ ግዴታ አለባቸው፡፡
11) የችሎት ታዳሚዎች እንዲሁም ተከራካሪዎች የወንጀል ድርጊትን የሚቀሰቅሱ ወይም በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ጽሁፎች ወይም መፈክሮች ያሉባቸውን ልብሶች ለብሰው ወይም በሰውነታቸው ላይ በመሳል ወይም በመነቀስ በችሎት እንዲታደሙ አይፈቀድም፡፡
12) በህኪም ከታዘዘለት ሰው በስተቀር አይኑ እንዳይታይ የሚያደርግ ወይም ጥቁር መነጽር አድርጎ ችሎት መግባት የተከለከለ ነው፡፡
13) ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ፣ ዐቃቢያነ-ህግ ወይም ጠበቃ ማንነቱን ሊደበቅ የሚችል ኮፍያ ወይም ጥምጥም ጠምጥሞ ችሎት መግባት የለበትም፡፡
14) ማንኛውም ሰው ፊትና አይኑ ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን ወይም ሰው እንዳያየው የሚያደርግ ልብስ ለብሶ ችሎት መግባት የለበትም

15) በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ክልከላዎች ቢኖሩም ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ፣ ጠበቃ እና ዐቃቢያነ-ህግ፣ ነገረ-ፈጅ፣ የአስተዳር ሰራተኞች ወይም ባለጉዳዮች በሀይማኖት ወይም በባሕል ምክንያት የሚለበሱ ልብሶችን ለብሶ ችሎት መግባት የሚችሉ ሲሆን ችሎቱ የተከራካሪዎችን ወይም የችሎቱን ባለጉዳይ ማንነት ለማጣራት ወይም ለማረጋገጥ ሲል ክብርን፣ ባሕልን እና ሀይማኖትን በማይጋፋ መልኩ ተደራቢ ልብሱን እንዲያነሳ ማዘዝ ይችላል፡፡

14. **የችሎት ሥራን አለማወክ**

1) ማንኛውም ሰው የችሎት ሥራን የሚያውክ ድርጊት በችሎት ወይም በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ መፈጸም የለበትም፡፡
2) ማንኛውም የችሎት ታዳሚ ወይም ባለጉዳይ ወደ ችሎት ከመግባቱ በፊት ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ወይም በድምጽ ሊያውኩ የሚችሉ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ድምጽ ማጥፋት አለበት፡፡

15. **ችሎቱን ስለማክበር**

ማንኛውም ሰው በሚከተሉት ሁኔታዎች ራሱን ዝቅ በማድረግ ለችሎቱ ያለውን ክብር ሊያሳይ ይገባል፣

1) ዳኛው ችሎት ሲሰየም እና ችሎት አስችሎ ሲወጣ፣
2) ዳኛ ተሰይሞ ሳለ ወደ ችሎቱ ሲወጣና ሲገባ፣
3) በችሎቱ አቋም ባይስማማም ዳኛው ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድ እና ውሳኔ አንብቦ ሲያጠናቅቅ፣

16. **የዳኞች መጠሪያ ስያሜ**

1) ማንኛውም ሰው ንግግር ሲያደርግ የፍርድ ቤቱን መሪ እንደ ቅደም ተከተላቸው በክብር ስማቸው ለሴት **«ክብርት»** ለወንድ **«ክቡር»** ኃላፊነታቸውንና ሙሉ ስማቸውን በመግለፅ እና ተገቢውን ክብር በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡
2) ማንኛውም ሰው በችሎት ውስጥ ወይም ከችሎት ውጪ ዳኛን ሲጠራ ለሴት **«ክብርት ዳኛ »**፣ ለወንድ **«ክቡር ዳኛ»** በማለት መሆን አለበት፡፡

17. **በግልፅ ችሎት ስለመዳኘት**

1) በዝግ ችሎት እንዲታዩ በህግ ከተደነገጉት ጉዳዮች በስተቀር ሁሉም ጉዳዮች በግልፅ ችሎት መካሄድ አለባቸው፡፡
2) ማኛውም ሰው የችሎቱን ሂደት የመከታተል መብት ያለው ቢሆንም የችሎቱ አዳረሽ የሚሞላ ከሆነ እንደ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል ችሎቱን እንዲታደሙ የተፈቀደላቸው መገናኛ ብዙሀን ጋዜጠኞች፣ ለተከራካሪ ወገኖች ቤተሰቦች እና በክርክር ላይ ባለው ጉዳይ ላይ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ጥቅም ላላቸው ሰዎች ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

18. **የቀጠሮ አሰጣጥ ሥርዓት**

1) ማንኛውም ዳኛ በጉዳዮች ፍሰት አስተዳር መመሪያ መሰረት ለጉዳዩ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መዛግብትን መቅጠር፣ ማስተናገድ እና እልባት መስጠት አለበት፡፡
2) ማንኛውም ዳኛ መዝገብ ሲቀጥር ጉዳዩ የሚታይበትን ሰዓት፣ ቀን፣ ወር፣ ጉዳዩን የሚያስተናግደው ችሎት እና የተቀጠረበትን ምክንያት በመዝገቡ ውስጥ ማስፈር አለበት፡፡

19. **በችሎት የተከለከሉ ድርጊቶች**

በችሎት ውስጥ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈፀም ከልክል ነው፡-

1) ዳኛው በችሎት እያስቻለ ችሎቱን በሚያውክ ሁኔታ የጎንዮሽ ወሬ ማውራት ወይም መሳቅ ወይም በስልክ መነጋገር፣
2) ድምፅ በሚያሰማ፣ እይታን በሚከለክል እና የሌሎችን ሰዎች ትኩረት በሚስብ መልኩ ጋዜጣና መሰል ጽሁፎችን ማንበብ፣
3) ከውሃ በስተቀር ሌሎች መጠጦችን መጠጣት፣ መመገብ፣ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣ ማስቲካ ማኘክ፣ መተኛት፣



Am/Nat/Regional State Supreme Court

4) ሌላ ሰው እንዳያልፍ በሚከለክል መልኩ እግርን ዘርግቶ መቀመጥ፣ በጠረጴዛ ላይ መቀመጥ፣ ሰው ወደ ችሎቱ እንዳያልፍ በተቀመጡ መከልከያዎች ላይ መቀመጥ፣

5) ቃጠሎ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን ይዞ መግባት፣ ጦር መሳሪያ፣ ዱላ ወይም ስለታማ የሆኑ መሳሪያዎችን መያዝ የተከለከለ ሲሆን ከልከላው የችሎት ሥነ-ሥርዓት አስከባሪን፣ ተጠርጣሪን ወይም እስረኛን አጅቦ የመጣን ፖሊስ ወይም በችግር ምክንያት ምርኩዝ ወይም ዱላ ይዞ የሚንቀሳቀስ ሰውን አይጨምርም፡፡

6) ከፍርድ ቤቱ አመራር እና ከዳኛው ፈቃድ ሲሰጣቸው የመገናኛ ብዙሀን ብቻ ችሎቱን በድምጽ፣ በምስል መቅረጽ እንዲሁም ፎቶ ማንሳት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ችሎቱን በተንቀሳቃሽ ስልክ፣ በካሜራ ወይም በቪዲዮ፣ ፎቶ ማንሳት፣ ምስል ወይም ድምጽ መቅዳት አይችልም፡፡

7) ሻንጣ እና ትላልቅ ቦርሳዎችን ወይም ለችሎቱ ሥነ-ሥርዓት የማይመች ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ማንኛውንም ዕቃዎች ይዞ ወደ ችሎቱ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

20. **ከዳኞች የሚጠበቅ ሥነ-ሥርዓት**

1) የችሎቱን ሥነ-ሥርዓት ማክበርና ማስከበር፣
2) የችሎቱን የዕለት መዝገብ መዘጋጀቱን፣ ባለጉዳዮቹ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣ መዛግብት እንደተቀጠሩበት ቅደም ተከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3) የሥራ ሠዓትን አክብሮ ችሎት መሰየምና መምራት፣ በበቂ ምክንያት ካረፈዱ ባለጉዳዮችን በማክበር ይቅርታ መጠየቅ፣
4) ለእለቱ ጉዳይ በቀረቡት መዛግብት ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
5) ዳኛ ወይም ሰብሳቢ ዳኛ ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ መምታት ችሎቱ ስለመጀመሩ ማብሰር፣
6) ዳኛ ችሎቱን ሲመራ የህዝቡን ባሕል፣ ወግ እና ሐይማኖት በማክበር መምራት፣
7) ለተገልጋዮችና ባለጉዳዮች ክብር መስጠት፤ ግራ ቀኙን በእኩልነት ማስተናገድ፣
8) ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች ችሎቱን የሚከታተሉ ሰዎችን አክብሮት በሚያሳይ መልኩ የሙያ ማዕረግ በመስጠት፣ አቶ ወይም ወ/ሮ፣ ወ/ሪት ወይም እርስዎ በሚሉት ቃላት መጥራት፣
9) በቀጠሮ ዕለት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ካልደረሰ ምክንያቱን ለባለጉዳዮች በመግለፅ ይህንኑ በመዝገብ ላይ በመመዝገብ ጉድለቱን የፍርድ ቤቱ ወይም የችሎቱ ወይም የዳኛው ከሆነ ይህንኑ ለባለጉዳዮች በመግለፅ በትህትና ይቅርታ መጠየቅ፣
10) የዳኝነት ፍትሀዊ አካሄድ መርህ በጠበቀ መልኩ ማንኛውም ባለጉዳይ ሀሳቡን ሳይሸማቀቅ በነፃነት እንዲገልፅ ማድረግ አለበት፡፡

21. **ከባለጉዳዮች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር**

ባለጉዳዮች የሚከተሉትን መተግበር አለባቸው፡-

1) በቀጠሮው ቀን፣ ቦታና ሰዓት መገኘት፣
2) በችሎት በተዘጋጀላቸው ቦታ መቀመጥ፣
3) በቀጠሮ ቀን ለክርክሩ በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረብ፣
4) ሌላኛው ተከራካሪ ሳይኖር ወደ ዳኛ ቢሮ አለመግባት፣
5) ችሎቱን ለማስከበር የሚሰጡ ትዕዛዞችን ማክበር፣
6) ክርክርን ወይም ተቃውሞን ወይም ሀሳብን ግልጽ አድርጎ ለዳኛ ወይም ለዳኞች በቀጥታ ማቅረብ፣
7) ክርክሩን ሲያቀርብ ወይም ዳኛው ሲያነጋግረው ዳኛውን ፊት ለፊት መመልከት፣
8) ክርክሩን ወይም ተቃውሞውን ወይም ሀሳቡን ሲያቀርብ ፍትሕን፣ እውነትን እና ማስረጃን መሰረት ማድረግ፣
9) የዳኛውን ስም ሳይጠራ «የተከበረው ፍ/ቤት» ወይም «ክቡር ዳኛ» ወይም «ክብርት ዳኛ» በማለት መጥራት፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት Am/Nat/Regional State Supreme Court North Shoa High Court

10) የችሎቱ ሥነ-ስርዓት እንዳይጣስ የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት፣
11) ምስክሮቻቸው ስለመቅረባቸው ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ማረጋገጥ፣
12) ምስክሮቻቸው ማንነታቸውን እና አድራሻቸውን በትክክል የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ይዘው እንዲቀርቡ ማድረግ፣
13) ምስክሮችን ከብራቸውን ጠብቆ ማናገር ወይም ጥያቄ መጠየቅ፣
14) ትዕዛዝ፣ብይን ወይም ፍርድ ወይም ውሳኔ ሲነበብ እስከመጨረሻው በጸጥታ እና በሥነ-ሥርዓት መስማት፤
15) ሳል ወይም ጉንፋን ከያዘው ሁኔታውን ለችሎች በማሳወቅ በቅድሚያ እንዲስተናገድ መጠየቅ ወይም ከችሎት ውጭ ሆኖ ተራውን መጠበቅ፣
16) ነፍሰጡሮች፣ ህፃናትን የያዙ፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን ወይም በቂ ምክንያት ያላቸው ባለጉዳዮች ቅድሚያ እንዲስተናገዱ ችሎቱን ማሳወቅ አለባቸው፡፡

22. **የተከለከሉ ተግባራት**

ማንኛውም ባለጉዳይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም የለበትም፡-

1) ክስ፣ ብይን፣ ውሳኔ፣ ፍርድ፣ ቅጣት መነበብ ወይም ምስክር መስማት ከተጀመረ በኃላ ችሎት አቋርጦ መውጣት፤
2) በችሎቱ የተነገሩት ጉዳዮች ትክክል መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን በአይን ምልክት፣ በቅንድብ፣ በፊት ገፅታ ወይም በሌሎች ተገቢነት የሌላቸው ወይም አለመስማማትን በሚገልፅ አካላዊ እንቅስቃሴ ማሳየት ወይም ዞሮ መናገር፣ ከዳኛ ጋር መሟገት፣
3) በህክምና የተረጋገጠ እና በልዩ ሁኔታ በችሎቱ ካልተፈቀደ በስተቀር አዳራሽ ውስጥ መመገብ ወይም ከውሀ ውጪ መጠጣት ወይም ማስቲካ ማኘክ፣
4) በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢም ሆነ በችሎት ውስጥ ሲጋራ ማጨስ ወይም ጫት መቃም፣
5) በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ በችሎት፣ በዳኞች ጽሕፈት ቤት አካባቢ ዳኞችን በድምጽ መረበሽ ወይም ማወክ፣
6) ሳይፈቀድ መናገር ወይም ዳኛው ወይም ሌላኛው ተከራካሪ ወገን እየተናገረ ጣልቃ ገብቶ መናገር ወይም ንግግሩን ማቋረጥ፣
7) ግልፅነት የሚጎላቸውን ቃላት መጠቀም፣ ችሎቱን ሳይፈቅድ ከችሎቱ የሥራ ቋንቋ ውጪ በሌላ ቋንቋ መናገር ወይም አንዱን ቋንቋ ከሌላው ቋንቋ ጋር በመደባለቅ መጠቀም፣
8) የተለዬ ትርጉም በሚሰጥ ሁኔታ እጅን በማወናጨፍ፣ ጣትን ወደ ዳኛ ወይም ባለጉዳይ ወይም ታዳሚ እየጠቆመ እና መሰል ተገቢነት የሌላቸው አካላዊ እንቅስቃሴ በመጠቀም ማውራት፣
9) የሌላኛውን ወገን ሰብዕና በማዋረድ፣ በማስፈራራት፣ በማሸማቀቅ ወይም በማሸሚጠጥ ክርክር ማቅረብ፣
10) ክርክርን በቀጥታ ለችሎቱ ከማቅረብ ይልቅ ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ጋር የጎንዮሽ ንግግር ማድረግ፣
11) በመጠጥ ስካር ወይም በሱስ ተፅዕኖ ስር ሆኖ ወደ ችሎት መግባት፣
12) አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የህጻናት ማቆያ ስፍራ የሌለ ካልሆነ በስተቀር ህጻናትን ይዞ መግባት፣

23. **ከሬጅስትራር፣ ከችሎት አገልግሎት ባለሙያ እና ከአስተዳድር ሰራተኞች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር**

1) ለችሎቱ በቂ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች መመደብና በማንኛውም ሁኔታ ሲጓደል ችሎት ከመጀመሩ በፊት ማሟላት፤
2) የቀጠሮ መዛግብትን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለዳኛ አሟልቶ ማቅረብ፣
3) የችሎቱን ሥራ ሳያደናቅፉ ወይም ሳያውኩ መስራት፣
4) ባለጉዳዮችንም ሆነ የሥራ ባልደረባን በአክብሮት ማስተናገድ፣
5) በዳኛው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና ሥራ ላይ ማዋል፣

6) ለችሎቱ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ክርክር እየተካሄደ ዳኛውን፣ ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮችን ወይም ማንኛውንም ሰው አለማውራት፣
7) የፍርድ ቤቱን መዝገብ እና ሰነዶች በአግባቡ መያዝ፣ በወቅቱ ለችሎቱ ማቅረብ፣
8) ከችሎቱ ጋር በተያያዘ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት የአስተዳደር ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው መከታተል፣
9) ለችሎቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መሟላታቸውን መከታተል እና ተጓድለው ሲገኙም ማሟላት፣
10) ሚስጢር መጠበቅን ጨምሮ ከችሎት ፈቃድ እና እውቅና ውጪ ማንኛውንም አይነት ማስረጃ ወይም ደብዳቤ አለማያያዝ፣

24. **የቋንቋ አስተርጓሚ ኃላፊነት እና ተግባራት**

1) በእውነት ለመተርጎም በገባው ቃለ መሀላ መሰረት የትርጉም ሥራውን ያለአድሎ በአግባቡ ማከናወን፣
2) ባለጉዳዮችን በአክብሮት ማስተናገድ፣
3) የዳኛን ትዕዛዝ ማክበር፣መቀበል እና ሙተግበር፣
4) ፍርድ ቤቱ በሚያወጣው የአስተርጓሚዎች መመሪያ መሰረት ውስጥ የተገለፁትን ተግባራት መፈፀም አለበት፡፡

25. **የችሎት አስከባሪ ሰራተኛ እና የችሎት ፖሊስ ኃላፊነትና ተግባራት**

1) ማንኛውም ሰው የችሎት ሥርዓት እንዲያከብር ማድረግ እና የችሎት ሥርዓት ተጥሶ ሲገኝም ለዳኛ የማሳወቅ፣
2) ዳኛውን ሳይጨምር ወደ ችሎቱ የሚገቡትን ሰዎች በመፈተሽ ማስገባት፣
3) ዳኞች ከመግባታቸው አስቀድሞ ባለጉዳዮችን ወደ ችሎት ማስገባት፣
4) ለችሎቱ ታዳሚዎች ስለ ችሎት ሥርዓት ገለጻ ማድረግ፣ ስልክ እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ድምፅ እንዲያጠፉ ማሳሰብ፣
5) በዳኛው የሚሰጥ ትዕዛዝን ማክበር፣ መቀበል እና መተግበር፣
6) ባለጉዳዮችን፣ ምስክሮችን፣ ተከራካሪ ወገኖችን እና ችሎቱን የሚከታተሉ ሰዎችን ማክበር፣
7) በችሎቱ ካልታዘዘ በስተቀር ክርክር እየተደረገ ሳለ ጣልቃ በመግባት አለመናገር፣ አለመንቀሳቀስ ወይም ሌሎች የችሎት ሥርዓቱን እንዳያደናቅፉ ወይም እንዳያውኩ ማድረግ፣
8) ለችሎቱ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከዳኞች፣ ከምስክሮች፣ ከባለጉዳይ እና ችሎቱን ከሚከታተል ማንኛውም ሰው ጋር አለማውራት፣
9) ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሚነበብበት ጊዜ በአንክሮ በማዳመጥ እንዲተገበር የበኩሉን ድርሻ ማበርከት፣
10) ዳኞች ችሎት ሲሰየሙ እና ችሎት አጠናቀው ወደ ጽህፈት ቤት ሲመለሱ ማጀብ እና ተገቢው ክብር እንዲያገኙ ማድረግ፣
11) ለዳኛው ሊቀርቡ የሚገቡ ሰነዶችን ዳኛው ሲፈቅድ ማቅረብ፣
12) የችሎቱን ፀጥታና ደህንነት ማረጋገጥ አለበት፣

26. **የችሎት ደህንነትን ስለማስጠበቅ**

የችሎት ድህንነትን የተሻለ ለማስጠብ እንዲቻል ማንኛውም ባለጉዳይ፡-

1) ወደ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት አዳራሽ ሲገባ በደህንነት ፍተሻ ስር የማለፍ ግዴታ አለበት፤
2) ዱላ፣ ስለት ወይም የጦር መሳሪያ በመያዝ ወደ ፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ ወይም የችሎት አዳራሽ መግባት አይችልም፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የፖሊስ እና የማረሚያ ቤት የፖሊስ አባላት እስረኞችን ለማጀብ የተሰጣቸውን ሕጋዊ የጦር መሳሪያ እንደያዙ ወደ ፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ መግባት አይከለከሉም፤ ሆኖም የጦር መሳሪያ ይዘው ወደ ችሎት አዳራሽ መግባት አይችሉም፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ቢኖርም ዳኛው የፖሊስ እና የማረሚያ ቤት የፖሊስ አባላት እስረኞችን ለማጀብ የተሰጣቸውን ሕጋዊ የጦር መሳሪያ እንደያዙ ወደ ችሎት እንዲገቡ የጉዳዩን እና የእስረኞችን አደገኛነት ከግምት በማስገባት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

27. **የችሎት ማጠናቀቂያ ሥርዓት**

1) ዳኛው ወይም ሰብሳቢ ዳኛው በችሎት ውስጥ የተገኙትን ሰዎች በማመስገን ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ በመምታት የችሎት ውሎው የተጠናቀቀ መሆኑን ማሳወቅ አለበት፡፡
2) ሥርዓት አስከባሪው ወይም ፖሊስ ለዳኛው ወይም ለዳኞች በወታደራዊ የሰላምታ ምልክት በማሳየት ዳኞችን እና በችሎቱ ላይ የተገኙ ሰዎችን በክብር መሸኘት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

28. **ችሎቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች**

1) ችሎቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ወይም ቅጣቶች ዓላማ ሰዎች በፈፀሙት ጥፋት ተፀፅተው ከጥፋታቸው እንዲማሩበት እና ሌሎችም እንዲማሩበት ማድረግ እንዲሁም የችሎቱን ክብር ማስጠበቅ ነው፡፡
2) ዳኛው ወይም ዳኞች የድርጊቱን አፈጻጸ፣ የፈጻሚውን ሀሳብ እና ስለሕግ ያለውን ግንዛቤ ግምት ውስጥ በማስገባት ወዲያውኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስዱ ይችላሉ፡-

ሀ) ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

ለ) ለተወሰነ ጊዜ ወደ ችሎቱ እንዳይገባ መከልከል፣

ሐ) ከችሎቱ ክፍል እንዲወጣ ማድረግ ወይም

መ) በወንጀል ወይም በፍትሐብሔር እና አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የችሎቱን ሥርዓት በመጣስ፣ በማወከ ወይም በማደናቀፍ ወንጀል ወዲያውኑ ፍርድ በመስጠትና ቅጣት መወሰን፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት በአስተዳደር ሰራተኞች ወይም የጉባኤ ተሿሚዎች ላይ የሚወሰድ እርምጃ ወይም ቅጣት አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

29. **የዳኛው ተጠያቂነት**

1) ማንኛውም ዳኛይህንን መመሪያ የመፈፀም እና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡
2) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከጣሰ በአማራ ክልል ዳኞች የሥነ-ምግባር እና የዲሲፒሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር 1/2017 ዓ.ም መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

30. **የፍርድ ቤቱ ተቋማዊ ኃላፊነት**

የበጀት ሁኔታ እና የፍርድ ቤቶችን አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ፍርድ ቤቶች፡-

1) ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ መመሪያውን በመገናኛ ብዙሀን፣ በቴሌቪዥን ወይም በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው፣
2) የችሎት አዳሾችን የሚሟላት ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3) የችሎት አዳራሾችን፣ የዳኞችን ቢሮ እና የዳኝነት አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን የሚያሳይ መረጃ በግልጽ በመለጠፍ ባለጉዳዮች እንዲያውቁት ማድረግ አለባቸው፡፡
4) የመረጃ ዴስክ አገልግሎት እንዲጠናከር እና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው፡፡
5) የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያዎች ላይ የተገለፁ የተቋማዊ ኃላፊነቶችና ተግባራት መፈፀም አለባቸው፡፡
6) ባለጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት ይዘው መግባት የማይፈቀድላቸውን የጦር መሳሪያዎችን የመሳሰሉ ንብረቶች የሚቀመጡበት የጥበቃ ቦታ ማዘጋጀት እና ለዚህም የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለባቸው፡፡

31. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**32. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ከተፈረመ ፤ (አንድ) ወር በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ህዳር 2018 ዓ.ም
ባህር ዳር

ዓለምአንተ አግደው ወንድሜነህ
የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት